ፓኖራማ ቁጥር 69

የትዝብት አድማስ

ግንቦት 2 ቀን 2001 ዓም

## ወንድቢ ለምን ራሱን በራሱ እያጋጨ ይሞታል?

ወንድቢ የሚባል ቀንድ ያለው የዱር እንስሳ አለ ። በብዛት የሚገኘው በምዕራብ ኢትዮጵያ ሱዳንን በሚያዋስኑ ክፍላተ-ሀገር ሲሆን ፥ በመንጋ ደረጃ በጎንደር ክፍለ-ሀገር በተለየም ደግሞ ጭልጋ አውራጃ ውስጥ በሽማለ-ጋራ፥በአርማጭሆ በአዳኝ ሀገር ጫቆና በወልቃይት ፀገዴ እንዲሁም በወለጋ ክፍለ-ሀገርና በኩታ ገጠም ወረዳዎች ይታይ ነበር ። በመሬቱ አቀማመጥና በአየር ንብረቱ ተስማሚነት የተነሳ በሰፊው ተራብቶና ተሰራጭቶ መታየቱና መታደኑ ያልተለመድ ክስተት አልነበረም ። ያካባቢውን አዋሳኝ መሬት የወያኔ መሪዎች ለሱዳን ካስረከቡ በኋላ ግን ወንደቢውም ከመሬቱ ጋር አብሮ ተሽልጎ ሄዷል ። ወንደቢው ከሀገሩ ወደ ባዕድ ሀገር ተሽልጎ በመሄዱ ምክንያት በደረሰበት ሀዘን ብቻ ሳይሆን፥ ከተፈጥሮ ባገኘው ባኅሪውም ጭምር፥ ሲያዝንና ሲበሳጭ እራሱን ከአለትና ከዛፍ ግንድ ጋር እያጋጨ በመዳጨር ራሱን ይገድላል። ይህም የሚሆነው ከዕድሜው ብዛት የተነሳ፥ ቀንዱ አርጅቶ ሲበሰብስ፥ በስብሶ ትል ሲያወጣ፥ትሉ ሲረባ፥ ትሉ ሲበላው፥ ሲያሳክከው፥ ሲያስፎክተው፥ ሲያቃጥለው ፥ መቆሚያ መቀመጫ ሲያሳጣው ፥ የራሱን ህይወት ራሱ ያጥፋል ። በደም አለባ እየተነከረ ፥ጭንቅላቱን በእልህና በቁጭት ከፊቱ ከሚያገኘው ነገር ጋር እያላተመ ይገድላል ። አዛኝም ይሁን ገላጋይ በማጣቱ ራሱን በራሱ ያጠፋል ። ገላጋይ በማጣት እጄን በእጄ በላሁት ዓይነት ነገር !

የወንደቢን ወደ ሱዳን ከኢትዮጵያ መሬት ጋር ተሽልጎ መሄዱና ሌሎቹም አራዊትና እንስሳት እንደዚሁ በመሰደዳቸው ምክንያት ፥ ባካባቢው ነዋሪዎች የተገጠሙትንና ለታሪክ ግንዛቤ በዜና መዋዕል መልክ የተመዘገቡትን ማስታወሱ አግባብነት ይኖረዋል ብለን እናምናለን። ለዚህም ሁለት ተዛማጅ/ ተደጋጋፊ ማስረጃዎቹን እናሰፍራለን።


Ethiopia will prevail !

1. “ተባብሮ መቋቋም፥ ተስማምቶም በመቆም ፥ የሀገሪቱን ሀብት ማዳን አቅቷችሁ ፥ አንበሳው ዝሆኑ ፥ ወንደቢው ፥ እንስሳት አራዊት አዕዋፋቱ ሁሉ ተሰደዱላችሁ:: ቀድሞ ነበር እንጅ ቆሞ መከላከል ፥ ያገር ሀብት ለማዳን ጠንክሮ መጋተር፥ አሁን ምን ይጠቅማል ከብቶቹ ከሄዱ ፥ ላሞች ከተነዱ ፈርስ ላይ መጓጎር ”

2. የኢጣሊያን ቅኝ ገዥዎች በ30ዎቹ ዓመት ምህረት ጎንደር ከተማ የተከሉትና ለነዋሪው ሕዝብ ለአራባ ዓመታት ያኽል የኤሌክትሪክ መብራት ሲሰጥ የቆየው የኤሊክትሪክ ኃይል ማመንጫ በወያኔ ትዕቢት ተነቅሎ ወደ ትግራይ በመሄዱ ምክንያት የሚከተለውን ስንኝ በሕዝቡ ተቀኝቷል::

“ ጣሊያን የተከለው የኮሬንቲው ሞተር፥ ጀግና በማጣቱ ተነቀለ ጎንደር :: ”

<u>የዛሬውን ርዕሳችን ስለ ወንደቢ ተፈጥሮና ባኅርይ ለመግለፅ ምክንያት የሆነን ፥ በወንደቢና በወያኔ መሪዎች መካከል የተፈጥሮ ሳይሆን ፥ የባኅርይና የድርጊት ተመሳሳይነት ስለአየንባቸው ነው:: ይህንም ባኅርይና ድርጊት ሊታይባቸው የቻለው፥ በግብታዊነትና በበአጋጣሚ አጋጣሚነት ሳይሆን፥ ወንደቢው ብዙ ዘመን በመኖሩ ምክንያት የውስጥ ደዌ ባስከተለበት ችግር የውስጥ ችግሩን መቋቋም አቅቶት ራሱን አጋጭቶ ራሱን ለማጥፋት መገደዱና ወያኔም በተመሳሳይ ሁኔታና ሂደት ራሱን እያጋጨ ራሱን ለማጥፋት በመጣደፍ ሂደት ላይ ያለ ቡድን መሆኑ ነው::</u>

በእንስሳነቱ ፥ የወደቢን ዕጣ-ፋንታ ስናይ ለማዘን ብንገደደም ፥ የወያኔ መሪዎች በሰብዓዊነታቸው ማንም ሳያስገድዳቸው ፥ ምንም ሳይቸግራቸውና አንዳችም ተፅዕኖ ሳይኖርባቸው ፥ በሀገራቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚያካሂዱት ውርደትና በድል ፥ ዕልቂት ፍጅትና ወንጀል ግን በማነኛውም ምክንያትና ዕይታ በቀላሉ ሊታይ የሚችል አይሆንም :: የበሰበሰው የወንደቢ ቀንድ ትል በመፍጠር በእንስሳው ላይ ሕይወትን እስከማጣት ድረስ ያስከተለበትን መከራና ስቃይ ፥ ከወያኔ መሪዎች ጋር ለማነፃፀር የቻለ ዜጋ፥ የነመለስ ዜናዊ የመጨረሻ ምዕራፍም በተመሳሳይ ሂደትና ድምዳሜ እንደሚገባደድ መገንዘብ አይቸግረውም :: ምክንያቱም፥ በአብዛኛው ሂደትና ይዘት ፥ የብዙዎቹ ተቃዋሚ ድርጅቶች መፈረካከስና መድከም የመጣው በራሳቸው ፥ በውስጣቸውና ዕርስ- በርሳቸው በሚፈጥሩት ችግር እንጅ ከውጭ በመጣ ጠላት ብቻ እንዳልተከሰተ የሚካድ አይሆንም ::



EthioLion.Com

በድቡሽት ላይ የተመሠረተ ቤት እንደማይቆም÷ዕርስበርሱ የሚፋጅ ሕዝብ ከድህነት አዘቅት እንደማይወጣ ÷ የተከፋፈለች መንግሥት እንደማትፀና ÷ ቅንቅን የበላው ትዳርም እንደ ማይሰነብት÷ታላላቅ የሃይማኖት መጽሕፍት በታሪክ እየመዘገቡት አልፈዋል።የወያኔ ዘረኛው ሥርዓትም ይህ ተመክሮ ከሚያመጣው ፍዳ ሊፀዳ አይችልም ። ይህ የዘረኞች ሥርዓት÷ ውስጡ በዕኩይ ባኅርይ ÷ በወንጀል ድርጊት÷በግፍና በጭካኔ÷በጥላቻና በበቀል÷ በፍርሀትና በስጋት ተሞልቶ እየተቦረቦረ ያለ ለመሆኑ ÷ በየጊዜው ከሚወስዳቸው ርምጃ መገንዘብ ይቻላል ። የፍርድ መጓደል÷ የሙስና ÷ የስካርና የወሲብ ÷ የአድሎና የበደል ÷ የግድያና አፈና÷የመሰሪነትና ጮሌነት÷ የወያኔ መሪዎችን ጭንቅላት ሞልቶ እያበሰበሰው ይገኛል ። የወንደቢው ቀንድ በትል እንደተሞላ ሁሉ ÷ የወያኔ መሪዎችም ጭንቅላት በመርዛማ ጋዝ ተሞልቷል ። የሳይንስ ጠበብቶች እንደሚያስረዱት ከሆነ መርዛማ ጋዝ ማለት ካርቦን-ሞኖክሳይድ ÷ ለሰው ልጅ አዕምሮና አካል መቅሰፍት ነው።ይገላል። ሞትን እንጅ ህይወትን አያመጣም ። በአዳኞቹ ቆስሎ የሚሸሽ ተቅበዝባዥ አውሬና በመርዛማ ጋዝ አዕምሮው የተመላ ሰውም ሆነ ሥርዓት መጨረሻው መሞትና መጥፋት ነው ። ይህንን የታሪክ ሂደት ÷ ማነኛውም መድኃኒት አያድነውም ። የወታደር ብዛት÷ የጦር መሳሪያ ክምችት ÷የሰላዮች ስምሪት÷ የፕሮፓጋንዳ ስርጭት ÷ የውጭ ርዳታ ÷ የገንዘብ ጋጋታ ጭራስ ሊያድነው አይችልም ።ያማ ቢሆን ኖሮ ከደርግ የበለጠ ሁሉን አሳክቶና አሟልቶ የነበረው አልነበረም። የወያኔ መሪዎች ይህንን ሀቅ እንዲገነዘቡ ተከታዮቻቸውና ረዳቶቻቸው÷የጡት አባቶቻቸውና አሽቃባጮቻቸው ለምን እንደማያሳስቧቸው ያስገርማል። ወያኔ ሲጠፉ ተያይዘን እንጠፋለን የሚል ኪዳነ- ሳጥናኤል ከሌለ በስተቀር!

“ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል” የተባለውን ይትበኃል መሠረት በማድረግ÷እየዘረፍን በመብላት እኛ እተየተጠቀምን ወገን መጥቀም ከተነሳንባቸው ዓላማዎች መካከል ዓይነተኛው ነው ። ይህንን ሳናደርግ ብንቀር “ሞኝ አሳላፊ ዘመዱን ይጎዳል” የሚል ተረት ይተረትብናል ። የሀበሻ ይሉኝታ ÷ የጎሊና ወቀሳ ÷ በታሪክ ተጠያቂነት÷ የትውልድ ፍርድ÷ የሞራል ልዕልናም ሆኑ ሌሎች የሰብዕና ጥያቄዎችና የመሳሰሉት ዝባዝንኪ ሁሉ÷ ለእኛ ሸተክ-በትክ ናቸው ብለው የደመደሙ ግለሰቦች ናቸው ከምንሊክ ግቢ የተሰባሰቡት ዛሬ ። በዚህ ዓይነት የነቀዘ ሥነ-አዕምሮ ውስጥ ስለሚኖሩ ÷ የማታ ማታ የነቀዘው አዕምሯቸው÷ የወንደቢን ዓይነት መጨረሻ እንደሚዳርጋቸው የታወቀ ነው። አዕምሯቸውን በመመረዝ ከወገናቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሲያቆራርጧቸው የከረሙት÷ ምዕራባውያን አለቆቻቸውም÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከራው ፅዋ ሞልቶ መገንፈሉን ሲያዩ÷ እንደነጋበት ጅብ ጥለዋቸው እንደሚፈረጥጡ በታሪክ የተረጋገጠ ሀቅ ነው ። ምክንያቱም ÷ የምዕራባውያን ፖሊሲ የተመሠረተው በንግድ ጥቅም ላይ በመሆኑ ነው ። ከዚያ በኋላ

ወያኔዎቹ፥ “ ነጋዴ ነህ ላካ እኛስ አንነግድም፥ ወረቱ ካለቀ ሰው አይወደድም ። ” እያሉ እንደ ወንደቢ እራሳቸውን እያጋጩ እራሳቸውን ማጥፋታቸው አይቀርም ። ምልክቱም ይኸው እየታየ ነው።

በዕምነት ፀንቶ መታገል የድል ዋስትና ነው !!!!

EthioLion.Com